# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

የዘጠነኛ እሑድ ሰንበት (የበዓለ ሃምሳ ሳምንት እሑድ ዘጰራቅሊጦስ)

ዘመነ ጰራቅሊጦስ የሚባለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ከተነሳ ከሃምሳኛው ቀን ጀምሮ እስከ ሰኔ ፲፯ ቀን ድረስ ያለው ነው። በእነዚህ ሳምንታትና ዕለታት የሚዘመረው መዝሙር የመንፈስ ቅዱስን መውረድ ትንሣኤን ዕርገትን የሚያነሣ ይሆናል።

## የዕለቱ ምስባክ

ዐርገ ውስተ አርያም ጼዊወከ ጼዋ
ወወሀብከ ጸጋከ ለእጓለ እመህያው
እስመ ይክህዱ ከመይህድሩ

ወደ ላይ አረግህ ምርኮንም ማረክህ
ስጦታንም ለሰዎች ሰጠህ
ደግሞም አመጸኞች በዚያ ያድሩ ዘንድ
መዝ ፷፯፥፲፰

ትርጉም፥(ዐርገ) ነፍሳትን ይዘህ ከሲኦል ወደ ገነት ወጣህ (ወወሀብከ) ለምእመናን ልጅነትን ሰጠሃቸው (እስመ ይክህዱ) ልጅነትን፣ መንፈስ ቅዱስን ባትሰጣቸው ይክዱህ ነበርና
(ኤፌ ፬፥፰ ። ቈላ ፪፥፲፭ ። ዕብ ፪፥፲፬)

ወንጌል፥ ዮሐ ፲፬፥፲፭-፳፩
ቅዳሴ፥ የዲዮስቆሮስ ቅዳሴ (እምቅድመ ዓለም)

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ዐርገ እምኃቤሆሙ አው (ወረደ መንፈስ ቅዱስ)
ከእርሱ ወደ ሰማይ አረገ ወይም መንፈስ ቅዱስ ወረደ

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ኤፌ ፬፥፩-፯ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፩ኛ ዮሐ ፪፥፩-፰ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፪፥፩-፬ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

## የዕለቱ ትምህርት

## መንፈስ ቅዱስ ለምን ወደ ዓለማችን በበዓለ ሃምሳ ወረደ?

### ኃይልን ለመስጠት
ድኩማን ኃይል ደቂቀ አዳም ይህን ዓለም በወንጌል ለመለወጥ ከአርያም ኃይል ያስፈልጋቸው ስለነበር ኃይልን ሊያለብሳቸው ነው የወረደው። «እነሆም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ» እንዳለ መድኃኒታችን፤ (ሉቃ ፳፬፥፵፱) በተጨማሪ የሐዋ ሥራ ፩፥፰ን ይመልከቱ።

### ሐሰተኛውን ዓለም ለመውቀስ
«እርሱም መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል። ስለ ኃጢአት፤ በእኔ ስለማያምኑ ነው፤ ስለ ጽድቅም ወደ አብ ስለምሄድ ከዚህም በኋላ ስለማታዩኝ ነው፤ ስለ ፍርድም የዚህ ዓለም ገዥ ስለተፈረደበት ነው።» (ዮሐ ፲፮፥፰-፲፪) ተብሎ እንደተጻፈ።
አዎን በእውነተኛው ጌታ አለማመን፤ ድል ስለተነሳው ጠላት ውድቀት አለማወቅ በኢየሱስ ክርስቶስ ወደቀደመ ክብር መመለስን አለማመን በደል ስለሆነ ይህንኑ ግልጽ አድርጎ ለመውቀስ ነው የመጣው።

### ወደ እውነት ሰዎችን ለማድረስ (ለመምራት)
«ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና የሚመጣውንም ይነግራችኋል» ይለናል ጌታ (ዮሐ ፲፮፥፲፫) ዘማሪውም ወደ ጽድቅ ምድር ይመራናል ይላል (መዝ ፻፵፪፥፲) እንዲሁም ወደ ንስሐ መንገድ ኃጢአተኞችን ያመራል (መዝ ፲፬፥፰) በክርክር ጊዜም እውነቱን ይገልጻል (ማቴ ፲፥፳-፳፫) መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን መርቶ ያደረሰበት እውነትም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። (ዮሀ ለ4፤6 ። 1ኛ ቆሮ ለ2፤3)

### ለማጽናናት ወረደ
ዓለም ኃዘንተኛ ስለሆነ ሊያጽናና ሐዋርያትም ከኢየሱስ ክርስቶስ ተለይተው መኖር ስለማይችሉ ስለ ወንጌል የሚገጥማቸው ፈተናም ብዙ ስለሆነ ለማጽናናት መጣ (ዮሐ ፲፬፥፲፮ ። ዮሐ ፲፭፥፳፮ ። ዮሐ ፲፮፥፭-፲፮) አልቃሻውን ዓለም ሊያጽናና ለመጣው ለእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ክብር ይሁን።

### ስለ ወልድ ለመመስከር
ዓለም ወልድን ስላላወቀው ስለ ወልደ እግዚአብሔር በሐዋርያት በቤተ ክርስቲያን አድሮ ለመመስከር ተገለጠ። (ዮሐ ፲፭፥፳፯ ። ፩ኛ ቆሮ ፲፪፥፫)

## መንፈስ ቅዱስ ወደ ዓለማችን በምን አምሳል ወረደ?

### በአውሎ ነፋስ አምሳል ነው
«ድንገት እንደሚነጥቅ አውሎ ነፋስ ለሰማይ ድምጽ መጣ፤ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሞላው።» (ሐዋ ፪፥፪) ተብሎ እንደተነገረ መንፈስ ቅዱስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ የተገለጠው በዓውሎ ነፋስ አምሳል ነበር። በብሉይ ኪዳንም እግዚአብሔር በአውሎ ነፍስና በወጀብ ውስጥ መንገድ እንዳለው ተተንብዮ ነበር እንዲህ ተብሎ «እግዚአብሔር ትእግስተኛ ኃይሉም ታላቅ ነው፤ በደለኛውንም ንጹህ ነህ አይልም እግዚአብሔር በወጀብና በአውሎ ነፋስ ውስጥ መንገድ አለው ደመናም የእግሩ ትቢያ ነው» (ናሆም ፩፥፫)። እግዚአብሔር በነቢዩ የተናገረውን ትንቢት ለመፈጸምና ለማከናወን በአውሎ ነፋስ አምሳል ተገልጦአል። ነፋሱም የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ እንደሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተናግሮአል (ዮሐ ፫፥፰)። ከዚህ በተረፈ በነፋስ ለምን እንደተመሰለ በሌላ ክፍል እንመለከታለን።

### በአምሳለ እሳት ወረደ
መንፈስ ቅዱስ በንጹሐን ሐዋርያት ላይ የወረደው በአውሎ ነፋስ አምሳል ብቻ አልነበረም። እንደወርቅ ሊያጠራቸው በእሳት አምሳል ነበር እንጂ። «እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው» (ሐዋ 2፤3) የሚለው ቃለ እግዚአብሔር ግልጽ የሚያደርገው ይህንኑ ነው። እሳትም የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጦአል (ማቴ ፫፥፲፩)።

... ይቀጥላል

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ... አሜን።